የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF EDUCATION

ስ: +251 11 155 3133
ፓ. ሳ.ቁ 1367፣ አራዳ ክፍለ-ከተማ,
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
T: +251 11 155 3133
P.O. BOX 1367, ARADA SUB-CITY,
ADDIS ABABA, ETHIOPIA
www.moe.gov.et
www.facebook.com/fdremoe
@fdremoe
info@moe.gov.et

ቀን/DATE: ጥር 09 2016

ቁጥር/REF NO: 9/256/926/16

ለሁሉም የመንግስት ዩኒቨርስቲዎች

ውጭ ሀገራት ለሚገኙ ኢትዮጵያ ኤምባሲዎች

ባሉበት

ጉዳዩ፡-የውጭ የትምህርት ዕድል ጋር ተያይዞ ያሉ ችግሮች ላይ በድጋሚ ማብራሪያ ስለመስጠት፤

ሀገራችን የያዘችውን የዕድገት ጎዳና እውን ለማድረግ ሁለንተናዊ ብልፅግናዋን ለማረጋገጥ ሀገሪቱ ያላትን ውስን ሀብት በአግባቡ በመጠቀም ለሁሉም ሴክተር መስሪያ ቤት ዘመኑ የሚፈልገውንና የሚያስፈልገውን ብቁ የሰው ኃይል ለማፍራት አስፋላጊ መሆኑ ይታመናል። ከዚህ አንጻር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማቶቻችንን ውስጣዊ አቅም ለመገንባት ለመምህራን የተለያዩ የትምህርት ዕድል እየተመቻቸ በመሠጠት ላይ መሆኑ ይታወቃል። ሆኖም ግን የትምህርት ዕድሎቹ ያለውን ውስን ሀብት በአግባቡ በመጠቀም ላይ ያተኮሩ ባለመሆናቸው ሀብት ሲባክን ይስተዋላል።

ስለዝህ የሚሰጥ ማንኛውንም የትምህርት ዕድል ወጥ በሆነ መልኩ ለመከወን እና ለማስተዳደር የአሰራር ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ለአፈጻጸሙ የስኮላርሽፕ መመሪያ ቁጥር 916/2014 ተዘጋጅቶ ስራዎች እየተተገበሩ ይገኛሉ። ነገር ግን አንዳንድ ተቋማት በውጭ ሀገራት ለሚማሩ ለሶስተኛ ዲግሪ ተማሪዎች የትራንስፖርት አሸፋፈን እና ኤምባሲዎች በውጭ ሀገራት ሙሉ ስኮላርሽፕ ድጋፍ ለሚማሩ (በኢትዮጵያ መንግስት ስኮላርሽፕ የማይደገፉ) ነገር ግን ተጨማሪ ድጎማ በኢትዮጵያ መንግስት ይደረግላቸው በነበረው አሰራር ላይ የሚከተሉት ማብራሪያሪ ቀርቧል።

1. በውጭ ሀገራት መንግስታት ሙሉ ስኮላርሽፕ ለሚማሩ ተማሪዎች ሲደረግ የነበረው ተጨማሪ ድጋፍን በተመለከተ

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ያሉ መምህራን አቅምን ለማሳደግ ተቋማት የተለያዩ የትምህርት ዕድሎችን መጠቀም እንደሚችሉ ይታወቃል። እነዚህ ዕድሎች መምህራን በግል የሚያገኙት፣ ተቋማት ከውጭ ሀገራት ተቋማት ጋር ባላቸው ስምምነት እና በትምህርት ሚኒስቴር በኩል የሚገኙ የነጻ ትምህርት ዕድሎች ሊሆኑ ይችላሉ። በመሆኑም በውጭ ሀገራት መንግስታት ሙሉ ስኮላርሽፕ ትምህርታቸውን በውጭ ሀገራት ለሚከታተሉ ተማሪዎች <u>የሚደረግ ተጨማሪ ድጋፍ የለለ በመሆኑን</u> (ለምሳሌ በህንድ ሀገር የICCR፣ በቻይና ሀገር የCSC፣ MoFCOM፣ በቱርክ፣ ሩሲያ እና ሌሎች ስኮላርሽፖች) ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ በትምህርት ሚኒስቴር ሲገለጽ የቆየ ነው። ይህንን ችግር ለመፍታት ተማሪዎች ከመሄዳቸው በፊት በተቋሞቻቸው በኩል እንዲያውቁ ማድረግ እንዲሁም ኤምባሲዎች መረጃውን ለተማሪዎች ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል። በኢትዮጵያ መንግስት በኩል ትምህርት ሚኒስቴር ለተቋማት ኮታ ሰጥቶ በማወዳደር መርጦ በህጋዊ መንገድ ደብዳቤ ሰጥቶ ውጭ ሀገር ለሚልካቸው ተማሪዎች ብቻ ሲደረግ የነበረው ድጋፍ በቀጣይም ዕድሉ ሲኖር በትምህርት ሚኒስቴር ተጋግጦና ተጣርቶ የትምህርት ዕድል በሚሰጥበት ወቅት ብቻ ትምህርት ሚኒስቴር ክፍያ የሚፈጽም ይሆናል። በመሆኑም በውጭ ሀገራት ወይም ተቋማት ውጭ ሀገራት ለሚማሩ ተማሪዎች የሚደረግ ተጨማሪ ድጎማ በትምህርት ሚኒስቴር/በኢትዮጵያ መንግስት የማይኖር መሆኑን በአግባቡ በመገንዘብ የነጻ ትምህርት ዕድል ስከላርሽፖችን ማስተዳደር ያስፈልጋል።

2. የትራንስፖርት ወጪ አሸፋፈን በተመለከተ

በውጭ ሀገራት ትምህርታቸውን ለሚከታተሉ የትምህርት ወጪው ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያ መንግስት የሚሸፍን ከሆነ የአውሮፕላን ትኬት የሚቀረጠው በኢትዮጵያ መንግስት ሆኖ ተማሪዎች፡-

*2.1 መጀመሪያ ለትምህርት ሲሄዱ*

*2.2 የምርምር ስራቸውን አጠናቀው የመመረቂያ ጽሁፎቻቸውን አስረክበው በኤምባሲ ደብዳቤ ወደ ሀገር ቤት ሲመለሱ እና*

*2.3 ለViva Voce ሲሄዱና ትምህርታቸውን አጠናቀው ሲመለሱ ይሆናል።*

በውጭ ሀገራት ትምህርታቸውን የሚከታተሉ የትምህርት ወጪው ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል በሌላ ሀገር ወይም ተቋም የሚሸፍን ከሆነ ስፖንሰር አድራጊው ሀገር/ተቋም



በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

የትራንስፖርት ወጪ የማይሸፍን መሆኑ ከተቋማቱ/ኤምባሲዎቻቸው እና ከሚመለከታቸው ተቋማት በማጣራትና በማረጋገጥ ተማሪዎች <u>ለትምህርት ሲሄዱና ትምህርታቸውን ሙሉ በሙሉ አጠናቀው</u> በኤምባሲ ደብዳቤ ወደ ሀገር ቤት ሲመለሱ የአውሮፕላን ትኬት <u>ለአንድ ጊዜ ደርሶ መልስ</u> ብቻ የጉዞ ትኬት የሚቆረጥላቸው መሆኑን እንገልፃለን።

ከሠላምታ ጋር

አብ ሚጀና (ዶ/ር)
የአካዳሚክ ጉዳዮች ዋና
ስራ አስፈፃሚ

ግልባጭ

- ✓ ለክቡር ሚኒስትር ጽ/ቤት
- ✓ ለከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት
- ✓ ለአካዳሚክ ጉዳዮች መሪ ስራ አስፈፃሚ
- ✓ ለመምህራንና ተማሪዎች ልማት ዴስክ

<u>ትምህርት ሚኒስቴር</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education